# ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም

ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ነች ማርያም ማለት፡-

ማ፡ የሚለው ቃል ማህደረ መለኮት የሚለውን ይፈታልናል። ይኸውም አምላክ በርሷ አድሮአልና መልዓኩ ቅዱስ ገብርኤልም ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብሏልና ሉቃ 1፤35 መለኮት ያደረባት ስለሆነች ይህ ትርጓሜ ተሰጥቷታል።

ር፡ ርግብየ ይቤላ ርግብ የዋህ እንደሆነ እርሷም በየዋህነቷ የተጠማውን ውሻ አጠጥታለች እንዲሁ ጭንቅ ሆኖባቸው የነበሩትን በዶኪማስ ቤት ወይን ጠጅ አልቆባቸው የነበሩትን በልጇ ተአምራት እንዲፈፀም ልጇን ጠይቃ የሠርገኞቹን ጭንቀት አስወግዳለች ዮሐ2፤1-11

ያ፡ ያንቃዐዱ ኃቤኪ ወዳንቺ ያንጋጥጣሉ ይማለላሉ ማለት ነው። እነሆ ፍጥረት ሁሉ በመድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ከዘላለም ሞት ድኖ ሳለ ከበደል ስላልራቀ የወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያምን ልመና ትሰፋ ያደርጋልና። አማላጅነቷን ይሻልና ለዚህም ነው መዝሙረኛው ዳዊት አሕዛብ ሁሉ በፊትሽ ይማለላሉ (ይለምናሉ ማለት ነው።) መዝ 44፤9

ም፡ ምሳል ወምስጋድ ሊሰገድላት፣ ልትከበር ይገባታልና የምትከበር፣ ሊሰገድላት የሚገባ እናት መሆኗን ለማመልከት ነው። ይኸው ድንግል ማርያም ወደ አክስቷ ኤልሣቤጥ ጋር በሔደች ጊዜ ፅንሱ በማህፀኗ እንደዘለለ ይነግረናል። ይህ ዘለለ የሚለው እንጣጥ እንጣጥ አለ ሳይሆን ሰገደ የሚል ፍቺ ያለው ነው። ሉቃ1፤44 የሰላምታዋ ድምጽ ደስታን የሚያጎናጽፍ ነውና።

## 2.1 ወላዲተ አምላክ ስለመሆኗ

ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መሆኗን እናምናለን። ይኸውም ወልደ አብ ኢየሱስ ክርስቶስን በገብረ መንፈስ ቅድስ በስጋ በዘመን ወልዳዋለችና። የተዋህዶ እምነትና ድንግል ማርያም ወላዲተ አመላክ መሆኗን ማመን የተያያዘ ነው። ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑን ጥቅሶች እንመልከት ምክንግያቱም ድንግል ማርያም እንደ ማህደር ተጠቀመባት እንጂ ወላዲተ አምላክ አትባልም ብለው ስለሚከራከሩ።

- ኢሳ 7፤14 "እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች"

ይህ ቃለ የሚወለደው ሕፃን አማኑኤል ተብሎ ይጠራል። ወላዲቱም ድንግል ናት ካለን ከፍ ብሎ እንዲህ ይለናል "እርሱም አለ እናንተ የዳዊት ቤት ሆይ ስሙ በውኑ ሰውን ማድከማችሁ ቀላል ነውን አምላኬን ደግሞ የምታደክሙ ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል" ኢሳ 7፤13 ይህን ቃል ልናጤነው ይገባል። የእስራኤል ቤት ብቻ ሳይሆን አለሙ ሁሉ ለመትረፍ በሰው ድካም አልሆነም። አሁን ግን አምላክ ሊደክም የኛን መከራ ተሸክሞ



ሊያድነን መጣ። እርሱም ምለክት ሰጠን ምልክታችንም ድንግል ማርያመ ነች፡ አምላኬን ደግሞ የምታደሙ ያለው ከድንግል የሚወለደው አምላክ መሆኑን ለማመልከት ነው። ወላዲቱም ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ያልናት ለዘህ ነው። አግዚአብሔር የሁላችንም በደል በእርሱ ላይ አኖረ ይለናል። ኢሳ 53፤6 አምላክ ሕመማችንን ተሸከመ የምንለው ለዚህ ነው።

- ኢሳ 9፤6 "ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናል አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘላለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።"

ሕፃን ተወልዶአል እርሱ ደግሞ ኃያል አምላክ ነው። ስለዚህ ወላዲቱ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ እንላታለን። ይኸም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሳ ነፍስ ነስቶ በፈጹም ተወህዶ ከብሮ ተወልዶአልና።

- ሉቃ 1፤43 "የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል"

አስተውሉ ሥራው የመንፈስ ቅድስ ነው። ኤልሳቤጥ አክስት መሆኗ እንጂ ድንግል ማርያም የጌታ እናት ትሁን አትሁን የምታውቀው ነገር የለም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ቲሞልታ ስለነበር የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆናል ስትል የጠየቀች ለዚህ ነው። መንፈስ ቅዱስ የተሞላ ድንግልን ያውቃታል፣ ያከብራታል፣ ያመሰግናታል እርሱ ጌታ ነውና ወላዲተ እግዚዕ እርሷ ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክ ያልናት ለዚህ ነው።

- ዮሐ 1፤14 "ቃል ሥጋ ሆነ ፀጋንና ክብርን ተመልቶ በኛ አደረ" ያ ቃል ይለናል መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐ 1፤1 ላይ "እግዚአብሔር ነው"

ስለዚህ የተወለደው የኛን ሥጋ የተዋሀደውን ክርስቶስ ኢየሱስን በሥጋ የወለደችው ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ ያልናት ለዚህ ነው።

- ገላ 4፤4 "ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ" ሴቲቱ ወላዲተ



www.ethiopianorthodox.org

አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ነች። የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከድንግል ተወልዶአልና ወላዲተ አምላክ ተበላ ትጠራለች።

## 2.2 በወላዲተ አምላክ ላይ ሰይጣን ያስነሳው ተቃውሞ (ጠላትነት)

በአባቶቻችን ትምህርት መሠረት ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም አለም ሳይፈጠር በአምላክ ልቦና ታስባ ትኖር ነበር። ይህም እንዲሁ የተናገሩት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አለው። እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በኋላ በክቡር ገነት አኖረው። ዘፍ 2፥8 ነገር ግን በክብር የተቀመጠው የሰው ልጅ የአምላኩን ሕግ በመተላለፍ ስሕተትን በፈፀመ ጊዜ ወደ እነሱ የመጣ የእግዚአብሔር ቁጣ ነበር እግዚአብሔርም እንዲህ አላቸው። "እግዚአብሔር አምላክም እባቡን አለው ይህን ስላደረግህ ከእንስሳት ከምድር አራዊትም ሁሉ ተለይተህ አንተ የተገረምህ ትሆናለህ በሆድህም ትሄዳለህ በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋ መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ" ዘፍ 3፥14-15 እባብ የተባለው በመጀመሪያ ሥጋ ለተሰጠው እባብ ሲሆን ፍፃሜው ግን ሁሌ ሰዎችን በማሳሳት ለሚኖረው ለሰይጣን ነው። እባብ ብሎ የሚጠራው ሰይጣንን ዘንዶውን እውሬውን ነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል። ስለወደቀው ስለ ተጣለው በመላዕከት ሰይፍ ስለተመታው ሲናገር "ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ" ራዕ 12፥9 ይለናል። ይህ የእባቡን ማንነት የሚገልጽ ሲሆን ሴቲቱ ያላት ደግሞ መደመሪያ ለሔዋን ሲሆን ፍፃሜው ግን ለድንግል ማርያም ነው። በአንተና በሴቲቱ መካከል ጠላትነት አደርጋለሁ ያለው መጀመሪያው በሔዋንና በእባብ በዘሮቻቸው መካከል ያለውን ጠላትነት የሚያሳይ ሲሆን ፍፃሜው ግን በሰይጣንና በድንግል ማርያም መካከል ያለውን ጠላትነት ነው።



ሰይጣን በድንግል ማርያም ላይ በጠላትነት የተነሣው እርሱን የሚቀጠቅጠውን አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር የሚገዛውን ወንድ ልጅ በመውለዷ እንዳሳደዳት ይነግረናል። "ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባለች ሴት ፊት ቆመ አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች" ራዕ 12፥4-5 ሰይጣን እርሱ ራስህን ይቀጠቅጥሃል የተባለው ክረስቶስ ከሴቲቱ ድንግል ማርያም በመወለዱ በቁጣ በጠላትነት በሴቲቱ- ላይ በድንግል ማርያዋ ላይ የተንቀሳቀሰው ለዚህ ነው። ዘንዶውም ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት። ራዕ12፥13 ለዚህም ነው ሰይጣን ራሱ እንዳይቀጠቅጥ ለሰው ልጆች አዳኝ የሆነ ክርስቶስ የደህንነታችን ምክንያት ሆኖ ድንግል ማርያም እርሱን በመውለዷ የአምላክ እናት በመሆኗ በታላቅ ቁጣ በሔሮድስ ላይ ተነስቶ እነዛን ሁሉ ሕፃናት ያስጨፈጨፈው በዚህ ጊዜ ከመልዐኩ ለዮሴፍ የተሰጠው ቃል "ሕፃኑን ሊገድሉት ይፈልጋሉና ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ" የሚል ነበር። ማቴ 2፥13 ለዚህም ነው በራዕ 12፥6 ላይ "ሴቲቱም ሺ ሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች" ያለን ይህም ጊዜ ሶስት አመት ከስድስት ወር ይሆናል። በስደት የቆየችባቸውን ወቅቶች ናቸው።

እርሱ ራስህን ይቀጠቅጥሃል የተባለ ክርስቶስ በዕለተ አርብ በተሰቀለ ጊዜ እሩቅ ብእሲ (ተራ ሰው) መስሎት ሰይጣን እንደለመደው ቀረበው። በተለይ "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሳበቅታኒ" አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ብሎ የአዳምን ጩኸት ሲጮህ ሰይጣን ሥጋውን በመቃብር ነፍሱን በሲኦል ለመቆራኘት መጣ። ያኔም አስጨንቆ ይዞ ቀጥቅጦ በመስቀሉ ሞት ከእግራችን በታች ጥሎታልና። ሰይጣንም አይሁዳውያኑና ሮማውያኑን በማስነሳት ፀዋተው መከራ በማብዛት ሰኮናውን ቀጥቅጦታል። ዲያብሎስ



www.ethiopianorthodox.org

አፈረ፣ የሞት ኃይል ተሻረ፣ ሙስና መቃብር በክርስቶስ ሞት ተወገደ፣ ተሸነፈ።

እንግዲህ ይህን ያደረገውን አምላክ በመውለዷ ሰይጣን ከአምላኩ ጋር ሳይሆን ውጊያው ጠላትነቱ ከድንግል ማርያም ከቅዱሳን መላዕክት ከቅድሳን ጋር ሆነ። በተለይም ሰይጣን በድንግል ማርያም ላይ በሌላው ፍጥረት የደረሰ የጥንተ አብሶ ወይም የአዳም የውርስ ኃጢአት በርሷ ላይ ስላልተገኘ በቁጣ በግኗል። ለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል። "እግዚአብሔር ዘር ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በጠፋን ነበር።" ኢሳ1፥9 ሰዶምና ገሞራ ሰው በማጣታቸው ዘር በማጦታቸው በመካከላቸው ንጹህ ዘር(ሰው) በመጥፋቱ በእሳት ዲን ተቃጥለዋል። ነገር ግን እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ዘር አስቀረለን የቀረችልን ዘር ከአዳም የውርስ ኃጢአት (Orginal sin) ከጥንተ አብሶ በደል የጸዳችና በእርሷ ያልደረሰባት ድንግል ማርያምን ነው። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን! ለዚህ ማረጋገጫ እንዲሆነን የመልዐኩ ቅ/ገብርኤል ምሥክርነት ይህ ነው። "ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ደስ የበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረከሽ ነሽ" ሉቃ1፥28 ጸጋው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞተ ጊዜ ስለኛ ደሙን ባፈሰሰ ጊዜ ከዘላለም ኃጢአት ከዘላለም ሞት እኛን ያዳነን ሲሆን ነገር ግን ድንግል ወላዲተ አምላክ ግን ከመውለዷ በፊት ገና ከመጀመሪያው ገና ስትፈጠር ፈጽሞ ይህ በደል ያልደረሰባት የእግዚአብሔር ጸጋ የጠበቃት የለያት ነች። ንጽህይተ ንጹሀን የምንለው ለዚህ ነው። ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ያላት እነደ ሴቶች ያለ ልማድ ፈጽሞ በርሷ ላይ አልመጣም አልደረሰምና ነው። እያንዳንዱ መልዐኩ የተናገረው ቃል የድንግል ወላዲተ አምላክን ክብር ንጽህና የሚገልጽ ቃል ነው።

የእግዚአብሔር ምስክርነት በዚህ ብቻ ሣያቆም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላችው ኤልሳቤጥ ይህንኑ ቃል በመድገም ተናግራለች "አንቺ ከሴቶች



መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።" ስትል ያንኑ የመልዐኩን ቃል ደግማለች ሉቃ1፥42

እንግዲህ ይህ ነው ሰይጣንን በቁጣ ቀስቅሶት በርሷ ላይ የጥላቻና የጠላትነት ቂሙን ለመወጣት ሰይጣን እስከ ዛሬ በተለያየ መንገድ የሚራወጠው። ከሰው ወገን ሥጋ ከለበሰው ፍጥረት ከድንግል ወላዲተ አምላክ በስተቀር ሌላው በጥንተ አብሶ ኃጢአት ምክንያት ተይዞ ያስጨንቅ የነበረው።እግዚአብሔር ባስቀረለን ዘር በድንግል ከጥፋት እንድንድን ምክንያት ሆናለች፡ ሰይጣንም እንደልቻላት ፈጽማም እንደማይችላት እንደተሸነፈ ባየ ጊዜ የውጊያውንና የጠላትነቱን አቅጣጫ በመቀየር የሚያከብራትንና በአማላጅነቷ የማይተማመኑ ሰዎችን መፍጠር ጀመረ። ልባቸውን እያሳወረ ክርስቶስን ያክል ጌታ ከማን እንደተወለደ እንዳያስተውሉና ይህንም አስበው እንዳያከብሩ የድንግል ፍቅር ከልባቸው ውስጥ በመፋቅ ተራ የሆነ እርሱ ሰይጣንን የሚያምነውን ብቻ በመተው ተቃውሞውን ቀጠለ። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይለናል። "ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩት ሊዋጋ ሄደ በባህር አሸዋ ላይ ቆመ ራዕ 12፥17 የባሕር አሸዋ ልል እንደሆነ የመናፍቃንም ልባና ጽኑ በእምነት የሚረጋ ስላልሆነ በባህር አሸዋ ይመሰላል። ስለዚህም በመናፍቃን ለቦና አድሮ ተቃዋሚ ሆኖ በድንግል ማርያም ላይ ተነሳ ጠላትነቱም ከዘርዋ በቀሩተ ላይ አደረገ ከዘሩዋም የቀሩት ማለት የእርሷን ገናናነት ክብርና አማላጅነት የተረዱትን የሚያምኑትን ሊዋጋ መንቀሳቀሱን የሚያመለክት ነው። ለዚሀም ነው እንግዲህ ቅ/ቤ/ክርስቲያናችንን ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ሁልጊዜ ሊፈታተናት የሚጥረው።"

ይኸውም ትልቁና አብይ ምክንያት የወንጌሉ ቃል ምን እንደሚል በትክክል መረዳት ባለመቻላቸው ነው። እውነተኛው የክርስቶስ የወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው የዚህ አለም ገዥ ልባቸውን አሳውሮታልና።



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም ወንጌሉ የምስራቹ የድንግል ማርያም ተቃወሚ አይደለምና። ወንጌሉ ክብሯን የሚናገር እንጂ የጌታ እናት ተቃዋሚ አልነበረም። እርሷን የሚቃወሟት ሁሉ ጌታን እየተቃወሙ ነውና። "የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል እናንተንም የጠላ እኔን ይጠላል እኔንም የጠላ የላከኝን ይጥላል" ሉቃ 10፥16 አስተውሉ ድንግልን የጠላ መልዐኩ ስለርሷ የተናገረውን ያልሰማ መንፈስ ቅዱስ በኤልሳቤጥ ላይ አድሮ የተናገረውን ያልሰማ እንዴት ጌታን ተቀብዬዋለሁ ሊል ይችላል? ድንግልን ጥሎአልና ጌታንም የጣለ መሆኑን ሊረዳው ይገባል። ወላዲተ አምላክነቷን እርሱ ብርሃን ነውና እመብርሃንነቷን ያልተቀበለ እንዴት ጌታ ሊኖረው ይችላል? ራሱን እንዲመረምር እንጠይቀዋለን።1ቆሮ 11፥31

## 2.3 የድንግል ክብርና ለርሷ የሚገባ ስግደትና አማላጅነቷ

ክብር ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ሲሆን አክባሪው እግዚአብሔር ነው። በተለያዩ ቦታዎችና ወቅቶች ጊዜዎች እግዚአብሔር ሰውን ያከብራል እግዚአብሔር ሙሴን እንደ አከበረው እንመለከታለን። ሙሴ የእግዚአብሔር ክብር ለማየት ጠይቆ እግዚአብሔርም አሳይቶታል። የእግዚአብሔር የክብር ብርሃን በሙሴ ላይ ስላረፈ የሙሴን ፊት ትኩር ብለው እንኳ ማየት አልቻሉም። ዘፀ 33፥17, ዘፀ 34፥28

ይህ ክብር የሚለው ቃል ጌትነትንና ከፍተኛነትን የሚያሳይ ነው። ከሁሉ በላይ ክብር ያለው እግዚአብሔር ነው ክብሩም በሥራው ይታያል። ዘጸ16፥7, 1ነገ 8፥11, መዝ 18፥1, እግዚአብሔር ክቡር በመሆኑ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ቅድስት ድንግል ማርያም አንዳች ያልጎደለባት ምልዕተ ጸጋ ስለሆነች እግዚአብሔርም ከርሷ ጋር ስለሆነ ክብርት ናት። እንኳን የአምላክ እናት ቅ/ድንግል ማርያም ምልዕልተ ፍጥረት የሆነች የእግዚአብሔር ፈጥረት ሁሉ ክቡር ነው። ሉቃ 2፥9 1ቆሮ 11፥7



ድንግል ማርያምን አስቀድሞ ያከበራት እግዚአብሔር ነው። ነቢያትም በትንቢታቸው ተናግረውታል እንዲሁ በራዕይ ዮሐንስ ም12፥1 "ፀሐይን ተጎናጽፋ ጨረቃ ከእግሮቿ በታች ያላት የአሥራ ሁለት ከወክብት አክሊል የሆነባት አንዲት ሴት ነበረች።" ይላል ይህ የሚያመለክተን የድንግል ማርያምን ክብር ነው። አክሊል የክብር ምልክት ሲሆን አስራ ሁለት ተብሎ መነገሩ በራሱ ዘንድ ያላትን ከፈተኛ ክብር ለመግለጽ ነው። ይህ ለድንግል ማርያም መነገሩን ወረድ ብሎ ስለሚመልስልን አከራካሪ አየሆንም። እንዲሁ መልዐኩ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበስራት "አንቺ ከሴቶች ሁሉ ተለየተሽ የተባረክሽ ነሽ ብሎአታል።" ሉቃ 1፥28 እንዲሁ በመዝሙረ ዳዊት መዝ 44፥17 "ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ" ብሎ እንደተናገረው ክብርት ስለሆነች ስሟ እስከ ዛሬ በትውልድ ሁሉ ይታወሳል ይመሰገናል። እንዲሁ ራሷ ወላዴተ አምላክ ቅ/ድ/ማርያም ስትናገር ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ሉቃ 1፥48 ላይ ተናገራለች ክብርት ስለሆነች እናመሰግናታለን ምስጋናችንም የሚገባ ነው። በሃይማኖት ለጸኑ ምስጋና እንዲበዛላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። "እንደ ተማራችሁ በሃይማኖት ጽኑ ምስጋናም ይብዛላችሁ" ቆላ 2፥7 ድንግል ሁሉን በልቧ በመጠበቅ ታኖረው ስለነበር ለልጇ ወዳጇ ካላት ፍቅር የተነሣ እግረ መስቀል ድረስ የተገኘች እናት ስለሆነች ምስጋና ሊበዛላት ስለሚገባ፣ ትውልድ ብፅዕት ቅድስት ሊላት ስለሚገባ እንደመጽሐፉ ትዕዛዝ እናከብራታለን እናመሰግናታለን።

እግዚአብሔር አምላካችን በድንግል በረከት ይጎብኘን

### 2.3.1 ለድንግል የሚገባ ስግደት

ስግደት አምልኮትን ብቻ ሳይሆን አክብሮትንና ሞገስን የሚገልጽ ጭምር ነው። ወደ እግዚአብሔር አምላካችን ስንቀረብ የምንሰግደው ስግደት ፈጣሪያችን አምላካችን ስለሆነ ነው። ስለዚህም ስግደቱ በአምልኮ የሚቀረብ ስለሆነ የአምልኮት ስግደት እንለዋለን። ወደ ድንገል ማርያም ስንሰግድ ግን



www.ethiopianorthodox.org

ፈጣሪያችን አምላካችን ብለን የአምልኮት ሳይሆን የጸጋ ስግደት ነው። ይህም ድንግል ማርያምን እግዚአብሔር ስላከበራት የምንሰግደው ነው እንጂ አምላክ ነች ፈጣሪ ነች ብለን አይደለም። ለምሳሌ ዩሐንስ መጥምቀ መለኮት ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ በደስታ ዘሏል። ይህም ስግደትን የሚያመለከት ነው። ሉቃ1፥44

- "ወንዶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ላይ ይሸከሙአቸዋል ነገስታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ። ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ።" ኢሳ 49፥22

ይህ መጀመሪያው ለጽዮን ሲሆን ድንገል እንደ ጽዮን ማደሪያው እርሷን ልዑል ቀድሷታልና በርሷም አድሮአልና ፍጻሜው ለድንግል ማርያም ነው። መዝ 45፥7

- "የእግሬንም ስፍራ አከበራለሁ የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ። የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ።" ኢሳ 60፥13

የእግሬን ስፍራ አከብራለሁ ማለቱ በርሷ ማህፀን በድንግል ማህፀን አድሮወልና ነው። አንሰገድም ያሉ ሁሉ በኋላ እንደሚሰግድላት ናገራል።

ሌላው እጅግ መታወቅ ያለበት ጌታ ከሰጠን ከአስርቱ ትዕዛዛት አንዱ "እናትና አባህን አክብር" የሚል ነው ዘፀ 20፥12 ታዲያ ወላዲተ አምላክ እኮ የጌታ እናት ነች እኛ ግን የጌታ ልጆች ነን በጣም ይህንን ልዩነት ልናጤነው ይገባል። ታዲያ እናት ስለሆነች ለድንግል መስገዳችን በእናትነቷ በተሰጣት ጸጋ የሰገድነው መሆናችንን እጅግ ሊረዱት የገባል። ልጇን አክብረን የአምልኮት ስግደት እንደምናቀርብ ሁሉ እንዲሁ እናትና አባትህን አክብር በሚለው መሠረት እናቱን አክብረን የጸጋ ስግደት ማቅረብ አለብን። ይህን እውነት ልንፍቀው አንችልም። ያልያ ግን ጌታ ፈሪሳውያንን እንደገሰጻቸው አይነት መሆኑ ነው። ማር 7፥11-13 ጌታ ከዚህ ያድነን።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ከላይ በትንቢተ ኢሳያስ ላይ ያየናቸው ጥቅሶች እንዴት ለድንግል ማርያም የተነገሩ መሆናቸውን እናውቃለን ይባል ይሆናል



መጽሐፍ ቅድስ እንዲህ ይለናል "ያም አለት ክርስቶስ ነበር።" 1ቆሮ 10፥5 ክርስቶስን በለሉይ ኪዳን አለት ሆኖ እናውቀውም ግን ምሳሌው ፍጻሜ ለክርስቶስ ሆኖ አለቱ እርሱ እንደሆነ ተነገረን። እንዲሁ በዕብ 9፥9 ላይ "ይህ በአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው" ይለናል በብሉይ የተነገሩት ሁሉ ለአዲስ ኪደን ጥላ በመሆናቸው የዛ ንግግር ፍጻሜ የት ላይ እንደተከናወነ የምናየው በአዲስ ኪዳን ነው። ደግሞም ስለ ጨዋይቱ ሣራና ስለ ባሪይቱ ሴት አጋር በአዲስ ኪዳን ያለው ምስርጢር ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን። ገላ 4፥21-1-31 እንዲሁ ሁሉ ስለጽዮን ታቦቷ ከነባራት አገልግሎት ጋር የድንግል ማርያም የአምላክ ማደሪያነት ጋር ተመሳሳይ ነውና። ስለጽዮን የተነገሩ ሁሉ ፍጻሜው ለድንገል ማርያም ሆኖ እናገኘዋለን።

እግዚአብሔር ማስተዋሉንና ጥበቡን ይግለጽልን

### 2.3.2 የድንግል ማርያም አማላጅነት

መልዐከ ብስራት ቅ/ገብርኤል ለድንግል እንዲህ ብሉአታል "ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ።" ሉቃ 1፥30 ጸጋ አግኝተሻል ሲል ክብር ሞገሰ መለመን የማስታረቅ ሃይል ማለት ነው። እስኪ ይህንን ጥቅስ እንመልከተው።

- "ራሳቸውም ስለ እናንተ ሲያማልዱ በእናንተ ላይ ከሚሆነው ከሚበልጠው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ይናፍቁአችኋል።" 2ኛ ቆሮ 9፥14

ይህ ስለ ቅዱሳን በሚሆን አግልግሎት ላይ ተነግሮአል። እነርሱም ሲያማልዱ ይለናል። እንግዲህ ቅድስተ ቀዱሳን የሆነች ድንግል ማርያም ምልጃን እንደምትፈጽም የሚናገር ነው። ከሚበልጠው የእግዚአብሔር ጸጋ በሎ እንደተናገረው ጸጋ አንዱ አገልግሎቱ የመለመን የማማለድ ኃይል መሆኑን ያሳውቀናል በግዕዙ ደግሞ እንዲህ ይላል። "ኢትፍርሒ ማርያም እሰመ ረከብኪ ሞገሰ በቅድመ እግዚአብሔር" በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ



www.ethiopianorthodox.org

አግኝተሻልና አትፍሪ ሞገስ ይህን ክብርን ማግኘትሽን ማማለድን በርሱ ዘንድ መስማትን ያሳየናል። በእግዚአብር ፊት ሞገስ ያገኘው ሙሴ እስራኤልን በዙ ገዜ ለምኖ አስምሮአል። ዘፀ 32፥8። መዝ 44፥9 "አህዛብ በፊትሽ ይማለላሉ" ይለምናሉ አማልጅን ይላሉ ማለት ነው።

- ዮሐ 2፥1-11 ይህን ቃል ስንመለከት ድንግል ማርያዋ ለምና ጭንቀታቸውን ማቃለሏን እንመለከታለን። ሠርገኞቹ ያለቀባቸውን ወይን ጠጅ በርሷ ልመና የጎደለው እንዲሞላ ተደርጓአል። ልኡለ ባህሪ ክርስቶስ ይህንን ሳያውቀው ቀርቶ አይደለም። ነገር ግን የእናቱን ክብርና ገናናነት ለመግለጽ ዝም አለ እንጂ። በዚህ ምዕራፍ ላይ በተለይ መናፍቃኑ የሚያነሱት ሃሳብ በቁጥር 4 ላይ ያለውን ነው። "አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ያለውን ያላዋቂ ሳሚ እንደሚሉት ጌታ እናቱን አልሰማትም እንደውም አላከበራትም የንቀት ንግግር ነው ይላሉ። በጣም ያሳዝናል። ይህ ንግግር እነርሱ እንደሚሉት ከሆነ "እናትና አባትህን አክብር" የሚለውን የራሱን ሕግና "እናትንነ የሰደበ ይሙት" የሚለውን ማር 7፥11 ላይ የተፃፈውን ሕግ ሽሯል ማለት ነው። ስለዚህ እንደነርሱ ትርጉም ከሆነ ነውርና ተንኮል የሌለበት ክርስቶስን ነውር አለበት ኃጢአት አለበት ሕግ ሽሯል ሊያሰኝ ነው። እርሱ ደግሞ "እኔ ሕግና ነቢያትን ለመሻር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ" ብሏል። ማቴ 5፥17 ፈጽሞ እርስ በርሱ የማይስማማ ፍቺ ይሰጡታል። በነሱ ፍቺ መሠረት ግን ጌታ ኃጢአት አለበት ያሰኛል። ለርሱ ክብር ምስጋና ይሁንና ልባቸውን ይመልስልን።

ፍቺው ግን በእኔና በአንቺ መካከል ምን ጥል አለ? ምን አለመግባባት አለ? የሚል ነው። ለምሳሌ በኛ የአነጋገር ልማድ ምን ችግር አለ እንላለን። ይህ ችግር ወይም ተቃውሞ እንደሌለው የምንገልጽበት ንግግር ነው። እንዲሁ በእስራኤላውያን ዘንድ ይህ አነጋገር የተለመደ ነበር። የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።



- "አንተ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ" 1ኛ ነገ 17፥18 ይህን አንዲት መበለት ኤልያስ በመጣ ጊዜ ልጇ ስለሞተባት የተናገረችው ነው። በመካከላቸው ምንም አይነት አለመግባባት አለመኖሩን ለመግለጽ ነው።
- "ንጉሡም እናንተ የጽሩያ ልጆች እኔ ከእናንት ጋር ምን አለኝ" 2ሳሙ 16፥10 ንጉሡ ዳዊት ይህን የተናገረው ልጁ አቤሴሎም በተነሳበት ጊዜ የጽሩያ ልጆች ስላስጨነቁት ነበር። ልጁንም ለመግደል በመፈለጋቸው። እኔ ምን በደልኳችሁ ልጄን አቤሴሎምን የምትገድሉት ለማለት የገለጹው አገላለጽ ነበር።

  በማቴ 8፥29 በማር 6፥1-9 ባለው ታሪክም ላይ አጋንንት "ካንተ ጋር ምን አለን ያለጊዜያችን አታጥፋን " እያሉ ሲናገሩ እንሰማለን።

እንገዲህ ይህ ንግግር ጥላቻን ንቀትን ሳይሆን የሚያሳየው ክበርን መውደድን ምንም አይነት ክፉ ነገር አለመኖሩን ፈቃደኝነትን የሚያመለክት ንግግር ነው።

"ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ማለቱ አዲሱን ወይን ደሜን ሰጥቼ ለዘላለም ሕይወት የምታገኙበት የመስጣችሁ ደሜ ጊዜ ገና ነው ማለቱ ነው። ሞቱን፣ ከሞቱ በፊት ባለች ጥቂት ጊዜ የሚሰጣቸው ሥጋና ደሙን ለመግለጽ ነው። ለዚህም በሉቃስ 22፥14 "ሰዓቱም (ጊዜውም) በደረሰ ጊዜ ከአስራ ሁለቱ ጋር በማዕድ ተቀመጠ እርሱም ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመኝ ነበር እላችኋለሁና" ጊዜዬ ገና አልደረሰም የሚለውን ለማስታወስ ነበር ስለዚህም የዚህ ቃል ፍቺ ይህን ወይን ደሙን የዘላለም ሕይወት የሚሰጠውን የሚሰጥበትን ጊዜ ለመግለጽ ነበር። እንግዲህ በአጠቃላይ ወላዲተ አምላክ ክበርት ንጸህይት ቅድስት የሁላችን አማጅ መሆኗን ተረድተን ብንማፀን ጌታ ይቅር ይለናል። ክብርን የሰጠ ጌታ ነው ከፍ ያደረጋት ጌታ ነው። እርሷ እናት ነችና ማንም የአምላክ እናት የለም



www.ethiopianorthodox.org

እርሷ ግን አብራ የተሰደደች ናት ለዚህም ነው የጌታ መልዐክ "ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ሽሽ" ያለው ማቴ 2፥13 እናም እንዲሁ ሲመልስ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ እንዲመለስ ተናግሮታል ማቴ 2፥19 ስለዚህም እያንዳንዳችን ሕፃኑ አለን የሚል ሁሉ ከእናቱ ጋር ሊይዝ ይገዋል። ሕፃኑን ይዞ እናቱን መተው አይችልምና እናቱ የሌለችው ሕፃኑ ክርስቶስ ሊኖረው አይችልም። ኦርቶዶክሳዊ ተወህዶ ሃይማኖታችን ግን ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዛ ትሔፋለች ሕፃኑን "አባታችን ሆይ" ብላ ስትጠራ እናቱን ደግሞ "በመልዐኩ ቅ/ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ" ብላ ትጠራታለች። "እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ" ብላ ሕፃኑን ስትጠራ "በእንተ ማርያም" ብላ እናቱን ትጠራለች። ስለዚህ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ስለምናገኘው ነው። ሕፃኑንና እናቱን ይዘን መሄድ የሚኖርብን።

## 2.4 <u>የእመቤታችን ዘላለማዊ ድንግልና</u>

ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም አባታችን ቄርሎስ እንደተናገረው ቅድመ ፀኒስ፣ ጊዜ ፀኒስ፣ ድህረ ፀኒስ፣ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ሕቱም ድንግል ናት ብሏል። ወደ አማርኛው ስንመልሰው ከመጽነሷ በፊት በፀነሰች ጊዜ ከፀነሰች በኋላ ከመውለዷ በፊት በወለደች ጊዜ ከወለደች በኋላ ድንግልናዋ ፍጹም ነው የሚል ነው። ከዚህ በመነሳት ስንመለከት ሕቱም ድንግል መሆኗን የሚያረጋግጡትን ጥቅሶች እንመልከት።

- "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች" ኢሳ 7፥14 ድንግል መጽነሷን ነገረን እንጂ ሌላ ትወልዳለች አላለም። ይህም ዘላለማዊ ድንግልናዋን የሚገልጽ ነው።
- ሕዝ 44፥2 "እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ የኖራል እንጂ አይከፈትም ሰዉም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል። አስተውሉ የትኛው የእስራኤል መቅደስ በር ነው ያልተከፈተው የነበረው እንደ መቅደስ እሱንም ከፍተው እየገቡ በአመት አንድ ቀን ያጥኑታል። በየጊዜውም ሊቀካህኑ ይገባል። ዕብ 9፥7 ይህ መቅደስ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ለድንግል የተነገረ መሆኑን ግን እንረዳለን። "በመካከላችሁ አድር ዘንድ መቅደስ ሥሩልኝ" እንዳለ ዘፀ 25፥8 እርሱ በመካከላችን ሆኖ የአብርሃምን ዘር ይዞ ሥጋ ለብሶ የተወለደው በመካከላችን ተገኝቶ ኃጢአትን ያስወገደው በድንግል ማሕፀን አድሮ ነው። ለዚህም ነው "እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ" ያለን ራዕ 22፥16 መቅደሱ ማደሪያው እንደነበረ እንዲሁ በድንግል አድሮ በድንግልና ተወለዶአልና። ከርሷም በነሳው ሥጋ ተገልጦ አምላካችን ሁላችንን አድኖናልና። ይህ በር ያለው ድንግልናዋን ነው ተዘግቶ ይኖራል ማለቱ ድንግልናዋ ዘላለማዊ መሆኑን ለማመልከት ነው። የእስራኤል አምላክ ገብቶበታል ማለቱ ክርስቶስ ኢየሱስ እርሱ አምላካችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በኀቱም ድንግልና ተወልዷልና ነው። ይህ ቃል ፍጹም ድንግልናዋን የሚያረጋግጥ ነው መጽሐፈ ቅዱስም "ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ" መዝ 45፥5 ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው። ስለቀደሳት ስለለያት ወደርሷ የገባ የለም።
- 2ቆሮ 11፥2 "እንደ ንጽህይት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና" ይለናል። ቅ/ጳውሎስ በኀቱም ድንግልና ስለፀናች እመቤታችን ድንግል ማርያም የመሰከረው ቃል ነው። በኋላ ላይ የተነሣውም ብርሃነ አለም ጳውሎስ ያረጋገጠው ድንግልናዋን ነው።

ነገር ግን እነዚህ የተባሉትን ጥቅሶች ባለማስተዋል ድንግል ማርያም ሌሎች ልጆች አሏት በማለት የናገራሉ። በመሠረቱ ቢኖሩ ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጹ ይነግረን ነበር። ፊደል ይገላል እንዳለ ፊደል ብቻ ይዞ በመሄድ መጻሕፍትን ካለመመርመርና የእግዚአብሔርን ኃይል ካለመረዳት የተነሣ የመጣ ስህተት መሆኑ ይሰማናል። ይህን የሚሉበትን ጥቅስ በሙሉ እንመለከተዋለን። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ፍቺውንም እንሰጣለለን። ማቴ 22፥29።




www.ethiopianorthodox.org

## 2.4.1 እጮኛዋ ዮሴፍ ለምን ተባለ?

እጮኛ የሚለው ቃልና ፍቺ ለሚያገባት ሴት ብቻ የተሰጠ ሳይሆን በጠባቂነትም ላለ ይሰጣል። ነገር ግን ድንግል ማርያም የዮሴፍ እጮኛ የተባለችበትን አንዳንድ ምክንያቶች እንመልከት።

✞ አንደኛው የዳዊት ልጅ ተብሎ ይጠራ ዘንድ ለዮሴፍ ታጭታለች።

ምክንያቱም በሴት ትውልዱ ቢቆጠር አይሁድ አይቀበሉም ማቴዎስ ትውልዱን ራሱ የፃፈው በዮሴፍ ነው። ለዚህም ነው መልዐኩ "ዮሴፍ ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት በአሰበ ጊዜ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ እጮኛህ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ" ያለው። ማቴ 1፡20 ሰባልነት ሆኖ ቢሆን ኖሮ ግን በስውር ሊተወት ፈጽሞ አያስብም ነበር። እንዲሁ እዛው ም1 ቁ.16 ላይ ስንሔድ በኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ የምናገኘው ዮሴፍን እንጂ ማርያምን አይደለም ይህ ለምን ሆነ? ተብሎ ቢጠየቅ የሚመልሱት መልስ የላቸውም። ነገር ግን የሁለቱ ዝምድና የጠበቀ ስለነበር ማቴዎስ የትውልዱን ቁጥር በዮሴፍ ጨርሶታል። ዝምድናቸውም በማቴ1፡15 ላይ ያለው አልዐዛር ነው።






በዚህ መሠረት ደግሞ ማንም ዘመድን ማግባት አይችልም። ዘሌ 18፡13-17 ስለዚህም ቅ/ድንግል ማርያም ለዮሴፍ እጮኛ የሆነችው የዳዊት ልጅ ተብሎ እንዲጠራ መሆኑ ግልጽ ለማድረግ ነው። ትውልድ መጽሐፉ የኢየሱስ ክርስቶስ ነውና።

✞ ሁለተኛው እንዲጠብቃት ነው ለዚህም ነው መልዐኩ የዮሴፍ ትቷት እንዳይሔድ የተናገረው

✞ ሶስተኛው እንዲያገለግላት ነው።

በስደቷ ጊዜ ይዞ እንዲሄድ የታዘዘው ዮሴፍ ነውና። ለሚስትነት ታጭታ ቢሆን ኖሮ ግን ከወለደች በኋላ ለዮሴፍ ሚስትህን ይዘህ ሂድ ይለዋል እንጂ ሕፃኑንና እናቱን ብሎ አይናገረውም ነበር። እንዳውም ከወለደች በኋላ ዮሴፍን እጮኛህንም ይዘህ ሂድ ሲለው እንኳን አንመለከትም ለዚህም ነው እንዲያገለግላት በእጮኝነት የተሰጠው ማቴ 2፡13 እና ቁ.19።

✞ አራተኛው ምክንያት እርሷ ከሦው ዘር ከሰው ወገን መሆኗ ይታወቅ ዘንድ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስም የአብርሃም ዘር ይዞአል ያለው ለዚህ ነው ዕብ 2፡15 ምክንያቱም እርሷን ኃይለ አርያማዊት ክርስቶስን መልዐክ ብለው የሚነሱ መናፍቃን አሉና። በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንዴት ትወልዳለች እንዳይሉ።

✞ አምስተኛው በዘፀ 5፡23 መሠረት "ሴት ወንድ ከጠገባ ሳይኖር ፀንሳ ብትገኝ ተወግራ ትገደል" የሚል ሕግ አይሁዳውያን ስላላቸው ተወግራ እንዳትገደል።

እነዚህ ብዙ ሌሎች ምክንያቶች አጮኛ አሰኝተዋታል እንጂ እጮኛነቱ ለመገናኘት ለባልና ሚስት ግንኙነት አይደለም። ስለዚህም ምዕመናን ይህን አውቀው የድንግል ክብር ለማቃለል ዘላለማዊ ድንግልናዋን የሚያድፈርስ ንግግር ለመናገር የሚሞክሩትን ሁሉ ማስረጃ በመስጠት አፍ ልናስይዝ ይገባናል እላለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

### 2.4.2 <u>የበኵር ልጇን እስክትወልድ ድረስ ማቴ</u> 1፡25

በኵር የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሶስት አይነት ፍቺ አለው።

1ኛ <u>የመጀመሪያ የሚል ነው</u>። ይህ የግድ ተከታይ ይኖረዋል የሚያሰኝ አይደለም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ "በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም የናቱን ማሕፀን የሚከፍት በኵር ሁሉ ለኔ ቀድስልኝ የኔ ነው።" ዘፀ13፡1 ይህ አገላለጽ መጀመሪያ ማሕፀንን የሚከፍት በኵር መባሉን ይገልጽልናል የግድ ተከታታይ ይኑረው እያሰኝም።

2ኛ <u>አለቃ የሚል ፍቺ አለው</u>። ለዚህም ማስረጃ ከመጽሐፈ ቅዱስ እንመልከት ዘፍ 49፡3 "ሮቤል አንተ በኵር ልጄና ኃይሌ የጉብዝናዬም መጀመሪያ ነህ <u>የክብር አለቃና</u> የኃይል አለቃ ...አለቅነትህ ለአንተ ይሁን" ስለዚህም በኵር የሚለው አለቅነትን ያሳያል። እንዲሁ ይህን ትርጉም የሚገልጽልን የያዕቆብና የኤሳው ታሪክ ነው። በዚህ ታሪክ ላይ ኤሳው ለምስር ወጥ ብኵርናውን ለወንድሙ ለያዕቆብ ሸጦለታል። በዚህም መሠረት በኵር ሆኖ በረከትን ከአባቱ ከይስሐቅ ተቀብሎአል። በወንድሙም ላይ አለቃ ሆኖአል። እግዚአብሔርም ራሱ ሲናገር "እኔ የአባቶቻችሁ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ" ያለው ለዚህ ነው። ነገር ግን ያዕቆብ ቅድሚያ በመወለዱ ሳይሆን አለቃ በኵር በሆኑ ያዕቆብ ከአባቶቹ ተደምሮአል። ይስሐቅ ለልጁ ለኤሳው ሲናገር እንዲህ ብሎታል። "ለወንድምህም ትገዛለህ ነገር ግን በተቃወምከው ጊዜ ቀንበርህን ከአንገትህ ትጥላለህ።" ዘፍ 27፡40, ዘፍ 25፡27-34

በዚህ መሠረት በኵር የሚለው ቃለ ሁለተኛ ፍቺ አለቅነትን ያሳያል ለምሳሌ በቆላ 1፡15 "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው" ሲል የመጀመሪያ ነው የሚል ፍቺ ሳይሆን ያለው አለቃ ነው። ከፍጥረት በፊት እርሱ አለቃ ነው አስቀድሞ የነበረው ነውና ራዕ1፡9



3ኛ <u>ተቀደሚ ተከታይ የሌለው</u> አንድ ብቻ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአስሔር <u>አንድያ ልጁን</u> እስኪሰጥ አለሙን እንዲሁ ወዷልና።" ዮሐ 3፡16 ይህ ቃል ልጁ አንድ ብቻ መሆኑን ሲነግረን ዕብ 1፡6 ላይ በኵር ብሎ ይጠራዋል። "ደግሞም <u>በኵርን</u> ወደ አለም ሲገባ የእግዚአብሔር መላዕክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ" ይላል። በኵር ብሏልና የግድ ተከታይ አለው ማለት አይደለም። ምክንያቱም የአብ አንድያ ልጅ ክርስቶስ ነውና እርሱም ተቀደሚ ተከታይ የሌለውን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በማቴ 1፡25 "<u>የበኵር ልጇን</u>" ሲል ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ልጇን ማለቱ እንደሆነ ልንረዳ ይገባል። በተለየ የዚህን ትምጉም በትክክል ባለመገንዘብ የተሳሳተ አመለካከትን ያባዛሉ። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱሱን በደንብ እንዲያጤኑት እናሳስባቸዋለን።

ከዚሁ ጋር በማያያዝ ከበኵር ጋር የሚገልጹት "ወንድሞቼ" ብሎ የተናገረውን ነው። እስኪ እርሱን ደግሞ እንመልከት እዚህ ላይ ማለት ማቴ1፡25 በኵር ያለው ከጥንተ አብሶ ኃጢአት በኋላ በአዲስ ፍጥረት ለመጀመሪያ ጊዜ የተወለደ ማለት ነው።

#### 2.4.2.1 <u>ወንዱሞቹ የሚለው ፍቺ</u>

- "ይህ የጸራቢው ልጅ አይደለምን እናቱስ ማርያም ትባል የለምን ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዩሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን እህቶሉቹስ ሁሉ በኛ ዘንድ አይደሉምን እንኪያስ የኸን ሁሉ ከወዴት አገኘው ተሰናከሉበትም።" ማቴ 13፡55-57
- ማቴ 12፡46 "ገና ለሕዝቡ ሲናገር እነሆ እናቱና ወንድቹ ሊነጋገሩ ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር።"

እነዚህ ጥቅሶች በመጥቀስ እመቤታችን ሌሎች ልጆች አሏት ይላሉ። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት ማቴ13፡55 ስናይ ይህ የጸራቢው ልጅ



www.ethiopianorthodox.org

አይደለምን?. ነው ያሉት እንግዲህ ወንድም የሚለው የግድ የሥጋ ወንድም መሆን አለበት የሚል ትርጉም ካገኘ የጸራቢው ልጅ ብለዋልና የዮሴፍ ልጅ ነው ማለት ነው። ግን ይህ እንዳልሆነ እናውቃለን። እነርሱም ጌታን በማጥላላትና በመናቅ የተናገሩት ነው ቃሉም እንደሚለን ተሰናከሉበት ስለሚል ዛሬ እነርሱ የተሰናከሉበትን ንግግበር ይዞ መጓዝ ያው እንደፈሪሳውያን መሰነካከል ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም አይሆንም ተሰናከሉበት ያለው ትክክል ስላልነበሩ ነውና። እንዲሁ አሁንም በዚህ መለኩ የሚጓዙ መናፍቃን በጌታ እየተሰናከሉበት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በጌታ የማይሰናከል የተባረከ እነደሆነ ተናግሮአል።

ከዚህ በመነሳት መጽሐፍ ቅዱስ ወንድች ለሚለው የሰጠውን ትርጉም እንመለከት

- ሀ. በአንድ ቤተሰብ ያሉ ወንድሞች ይባላሉ። ዘፍ 13፤8 እኛ ወንድማማች ነንና በእረኞቻችን መካከል ጥል እንዳይሆን ብሉ አብርሃም ለሎጥ ሲናገረው እናያለን። ነገር ግን ቀዳም ባለው ምዕራፍ ላይ በምዕ 12 አብርሃም ለሎጥ አጎቱ እንደሆነ እንመለከታለን።
- ለ. የሀገር ለጆች ወንድሞች ይባላሉ። ዘጸ 2፤11 እርስ በርሳቸው ሲደባደቡ ለነበሩ እስራኤላውያን ሙሴ የተናገራቸው ነበር።
- ሐ. የቅረብ ዘመዶች ወንድሞች የባላሉ ዘኁ 20፤14
- መ. እውነተኛ ወደጆች ወንድሞች ይባላሉ 2ሳሙ 1፤26
- ሠ. የአንድ ነገድ ልጆች ወንድሞች ይባላሉ 2ሳሙ 19፤11
- ረ. ቃል የሚገባቡ ሰዎች ወንድሞች ይባላሉ አሞ 1፤9
- ሰ. ከሃይማኖት አንድ የሆኑ ሰዎች ወንድሞች ይባላሉ። ሮሜ 1፤13 ፊል 1፤12 ወንድሞች የሚለው ቃል ብዙ ጥቺ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ስለሆነ ወንድም የተባለ ሁሉ የግድ በሥጋ ከአንድ እናትና አባት ተወልዶአል ማለት አይደለም። ለመሆኑ ይህን በድንግል ላይ የሚናገሩ እርስ በርስ "ወንድም ወንድም" ይባባሉ የለምን? ታዲያ እነዚህ ሁሉ



በስጋ የአንድ እናትና አባት ልጆች ናቸውን? "ማስተወል ከኃጢአት መራቅ ነው።" ኢዮ 28፤28 ይላልና። ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምንናገረው በትክክል ማስተዋል ይኖርብናል እንጂ በጎ ህሊና ከማጣት የተነሳ ነቀፋን ከመናገር የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ከመንቀፍ ልንቆጠብ ይገባናል "እምነትና በጎ ህሊና ይኑርህ አንዳንዶች ህሊናን ጥለው መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና።" 1ኛ ጢሞ 1፤19

## ለምን ወንድሞችህ ብለው ተናገሩ ለሚለው የሚከተለውን እንመልከት

አንደኛው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ወንድሞች እንደሚባሉ ሁሉ ክርስቶስ ከሠው ወገን እንደ አንዱ ሆኖ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ቀወስኖ የተገለጠው እንደተባለው ከጌታ ጋር ጭቃ እያቦኩ ወፍ እየሰሩ አፈር እየፈጩ ያደጉ አብሮ አደግ ጓደኞቹ የእመቤታችን የአክስቶቿ የአጎቶቿ ልጆች ናቸው ለምሣሌ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ሐዋርያው ያዕቆብ የጌታ ወንድም ይባላል። እናቱ ሶስና ወይም ማርያም ባውፍልያ የእመቤታችን ዘመድ ነበረች። የቅርብ ዘመዶች ወንድሞች ይባላሉና ዘኁ 20፤14

ሌላው ዮሴፍ ለድንግል ማርያም ሲታጭ ሚስቶቻቸው ከሞቱባቸው መካከል ስለነበር ዮሴፍ የቀድሞ ሚስቱ የሞተችበት ሰው ፈት (Widower) ስለነበር ከቀድሞ ሚስቱ የወለዳቸው ልጆች በመሆናቸው በቤት አብረው በማደጋቸው ወንድሞች ተብለዋል። እንግዲህ ከላይ ወንድሞች ተብሎ የተሰጠውን ጥቺ ለማየት ይህ ከምን አንፃር ለምን እንደተባለ ሊረዱት ይገባል እንላለን። ማስተዋልን የስጥልን።



www.ethiopianorthodox.org

### 2.4.3 እስከ የሚለው ፍቺ

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ "እስከ" የሌለው ቃል መጨረሻ የሌለው እስከ (Infiniste until) ነው። ቅዱስ መጽሐፍችን መጨረሻ የሌላቸውን ድርጊቶች በእስከ ያስቀምጣቸዋል። እስከ የሚለው ወቅትን መጠነ ጊዜን(Time interval) አያሳየንም። ምስኪ ይህን ሊያስረዱ የሚችሉ ጥቅሶችን ምንመልከት።

- 1ኛ ዘፍ 8፥7 "ውሃው እስከሚጎድል ድረስ ቁራው አልተመለሰም" እንደ እነርሱ አባባል ከሆነ ተመልሷል ያሰኛል ቁራው ግን ውሃውም ከጎደለ በኋላ አልተመለሰም። እስከመጨረሻው ማለት ነው።
- 2ኛ 2ሳሙ 6፥23 "ሜልኮም እስከሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ አልወለደችም" ይላል ሰው ከሞተ በኋላ ልጅ እንደማይወልድ እናውቃለን የጊዜ ገደብን ወቅትን የሚያሳይ ቢሆን ከሞተች በኋላ ወለደች ያሰኝ ነበር ነገር ግን እስከ የሚለው ቃል መጨረሻ የሌለው መሆኑን ያመለክታል።
- 3ኛ ማቴ 18፥22 "ኢየሱስ እንዲህ አለው እስከ ሰባ ጊዜ እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልህም" ጌታችንን ጴጥሮስ ስለይቅርታ ጠይቆት የሰጠው መልስ ነው። እስከ ብሏልና አባዝተን ወይ ደምረን የሆነ ቁጥር ድረስ ይቅር በለው ከዛ በላይ ይቅር አትበል ማለት አይደለም። መበደሉን አውቆ ይቅርታ የሚጠይቀውን ሁሉ እስከ መጨረሻው ይቅር ማለት እንደሚገባ ያሳያል። ነገር ግን እንደ ፕሮቴስታንቶቹ አገላለጽ ከሆነ ወንድምህን ይቅር ማለት ያለብህ እስከ ተወሰነ ቁጥር ነው ያሰኛል ይህ ደግሞ በምህረቱ ባለጠጋ የሆነውን እግዚአብሔርን ማሳዘን ይሆናል።
- 4ኛ ማቴ 28፥19-20 "እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ" አለም ከተፈፀመ በኋላ ከእነርሱ ይለያል ማለት ነውን? አይደለም እስከ ፍፃሜው ከእናንተ ጋር ነኝ ማለቱ ነው።



- 5ኛ ሮሜ 5፥14 "ከአዳም አንስቶ እስከ ሙሴ ሞት ነገሠ" ይህ እንደፕሮቴስታንቶቹ አገላለጽ ከሆነ ከሙሴ በኋራላ ሞት አልነገሠም ቀርቶአለ ማለት ነው ግን ይህ አይደለም።

እንግዲህ ከላይ ያየናቸው በሙሉ እስከ የሚለው ቃል መጨረሻ የሌለው መሆኑን ነው።

እስከምትወልድ ድረሰ አላወቃትም ነበር የሚለው እስከ መጨረሻው በግብር አላወቃትም የሚል ነው። ከዛ በኋበላ የሚል ፍቺ የለውም።

⇒ አንድም ሥራው ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ አላወቀም ነበር። ምክንቱም ማቴ 1፥19 ላይ በስውር ሊተዋት አሰበ ይለናልና።

⇒ ፍጡራንን ሁሉ የፈጠረ ክርስቶስ ያለ ዘር እንዲወለድ አላወቀም ሮሜ 3፥21

⇒ ከንጹህ ዘር የተገኘች ድንግል የእግዚአብሔር ማደሪያ እንድትሆን አላወቀም ሉቃ 1፥35

እነዚህ ፈቺዎች የያዘ እንጂ ፈጽሞ እነርሱ እንደሚሉት አይደለም። ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የሰው ወገን የሰው ዘር የሆነች የጥንተ አብሶ ኃጢአት ያልደረሰባት ያላገኛት የአምላክ እናት በነቱም ድንግልና ዘላለም ድንግል የሆነች እንደሆነ ሊታወቅ ይገባዋል።

### 2.5 የሁላችን እናተ ብጽዕት አመቤት

- መዝ 86፥4 "ሰው እናታችን ጽዮን ይላታል በውስጥዋም ሰው ተወለደ እርሱ ራሱ ልዑል መሠረታት።"

ይህ ስለ ድንግል ማርያም የተነገረ ትንቢት ነው ጽዮን የተባለችው ድንግል ነች ጽዮን የእግዚአብሔር ታቦት የእግዚአብሔር አድሮባታል በርሱም ሆኖ ያነጋገራቸው ነበረ። ዘፀ 25፥22 ድንግ ወላዲተ አምላክም እግዚአብሔር በርሷ ስላደረ በጽዮን ተመስላለች በውስጥዋ ሰው ተወለደ ይላል። በጽዮን ታቦት ውስጥ የትኛው ሰው ነው የተወለደው ብለን ብንጠይቅ



www.ethiopianorthodox.org

ስለ ጽዮን ታቦት እንዳልተነገረ እናስተውላለን። ጽዮን በተባለት በድንግል ማኅፀን ግን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶአል። ራሱ ልዑል መሠረታት እንዳለው እርሱ አጽንቶአታልና መሥርቶአታል፣ ፈጥሮአታል፣ አንጽቶአታል፣ ቀድሶአታልና በርሷ ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲወለድ ወደደ። ስለዚህም እኛ ድንግልን ወላዲተ አምላክን እናታችን እንላታለን።

- ዮሐ 19፤26 "ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ አላት ከዘህ በኋላ ደቀመዝሙሩን እናትህ እነኋት አለው።"

ይህ ቃለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ አማካኝነት የእርሱን እናት ለሁላችን እናት አድርጎ የሰጠበት ነው። እንግዲህ እኛ ከጌታ እንበልጣንን? የክርስቶስን እናት እናታችን ማለት ሲገባ ለርሷ ክብር ምስጋና ይግባትና በድፍረት እህታችን የሚሉ አሉ። በጣም ባይታደሉና ባያስተውሉ እንጂ ልጇን አምላካችን ብለንስንጠራ እናቱን እናታችን ብለን ልንጠራት የተገባን ለዚህ ነው። ቅ/ተዋህዶ ሃይማኖታችንም የቀራኒዮውን ሰው ክርስቶስ አምላካችን የሰጠንን ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በፈቱተች ቁጥር ከእግረ መስቀሉ ሥር የተገኘችው እናታችንን ታስታውሳለች። እርሷ ለሁላችን እናት ነችና።

እነኋት እናትህ እንዳለው ሁሉ እኛንም ልጆች አድርጎናል የቅ/ድንግል ልጆች፤ ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ በመልዕክቱ እንዲህ ያለው "ትዕዛዝን ከአብ እንደተቀበልን ከልጆችሽ በእውነት የሚሔዱ አንዳንዶችን ስለ አገኘኋቸው እጅግ ደስ ብሎኛል አሁንም እመቤቴ ሆይ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እለምንሻለሁ።" 2ዮሐ 1፤5 እኛም ለርሷ ልጆች አድርጎ እናት የሰጠን አምላካችን ነው።



በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው የተለያዩ እናቶች ልጆቻቸውን ከሞት፣ከጥፋት፣ ከባርነት ከሕመም ከደዌ እንደዳኑ ሁሉ እንዲሁ እናታችን ቅ/ድንግል ማርያም በምልጃዋ እያንዳንዳችንን ከሞት ከጥፋት ከሰይጣን ባርነት ከሕማም ከደዌ በልመናዋ ታድነን ዘንድ ጌታ እናት አድርጎ ስጥቶናልና። እግዚአብሔር የተመሠገነ ይሁን የእርሷን እናትነት ያልተቀበለ እንዴት የጌታን አምላክነት ሊቀበል ይችላል ወደ ማስተማዋል ሕሊናቸውን ይመልስለን። ለሁሉ የሚገባውን መስጠት የተገባ ነውና ሮሜ 13፤7፤ በእናቶቻቸው ጸሎት የተረፉትን ቀጥሎ ባለው ላይ ተመልከቱ ዘፍ 27፤42,1ኛ ነገ17፤17-24,2ኛ ነገ 4፤1-8, ማቴ 15፤21-28

## 2.5.1 ብፅዕት ናት በዚህ ላይ የሚነሱ ጥቃቄዎች

- ሉቃ 1፤48 "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል።" ድንግል ብፅዕት የተመሰገነች እናት ነች። ስለዚህም እኛም የትውልዱ ክፈሎች ነንና ብፅዕት ልንላት ይገባል።
- መዝ 44(45)፤17 "ለልጅ ልጅ ሁሉ ስመሽን ያሳስባሉ" እንደለ ስሟን ብፅዕት እመቤት እያልን ልናሳስብ ይገባናል።

ተጨማሪ በዚህ ላይ የሚነሱ ጥያቄች

- ሉቃ 8፤21 "እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉ እነዚህ ናቸው"

ይህ አገላለጽ እናቱን መንቀፉ ሳይሆን ያን ጊዜ ጌታ በማስተማር ላይ ነው። ስለዚህ ቃል እግዚአብሔርን ማቋረጥ ስለማያስፈልግ ይህን አለ። ይኸውም አባባሉ እናተና ወንድሞቼ እንደሚፈልጉኝ እንዚህን ቃሌን ለመስማት ይፈልጉኛል። የጌታም ዋና አላማ ወደዚ አለም የመጣው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስተማር ነው። ስለሆነም በዕረፍት



www.ethiopianorthodox.org

መምጣብም ማስተማርን አያቋርጥም ነበር ዮሐ 4፥31 ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው መልስ ከዚህ ጋር አንድ ነው እንጂ በድንግልና ፀንሣ በድንግልና የወለደችውን፣ አዝላ በረሃ ለበረሃ እሾህ እየወጋት፣ እንቅፋት እየመታት፣ ውሃ ጥም ረሃብ እያቃጠላት የተሠደደችውን እናቱን መንቀፋና አላውቅሽም ማለቱ አይደለም። ያውም እሱ ለሰው ልጆች እናትና አባትህን አክብር ዘፀ 20፥12 ብሎ ያዘዘ ነው። ታዲያ ጌታ ሕግ አፍራሽ ነውን? እንዲሁም ጌታ በመቅደስ እኔ ከሰማይ የወረድኩ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ እያለ ሲናገር ይህ ሰው ሰምቶ ስለ ነበር ለማሣጣት ፈልጎ ኑንቅ ብእሲ (ተራ ሰው) ነህ ለማለት እነሆ እናትህና ወንድሞችህ ፈልጉሃል ቢለው ጌታም በሰውየው ልብ ውስጥ ያለውን ክፋት ተመለክቶ ይህን መልስ ሰጥቶታል።

☞ ሉቃ 11፥27 "ይህን ሲናገር ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማህፀንና የጠባሐቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው። እርሱ ግን አዎን ብፁአንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው"

☞ እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባ ሴትየዋ የተናገረችውን ስሕተት ስላልነበር "አዎን" ብሎአታል። ልክ ነሽ የተሸከመችኝ ማኅፀንና የጠባኋቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው። ደግሞም ብፁዓን ሊሆኑ የሚችሉ አሉ። ትክክል ናትና አዎን ብሏታል። ይህቺ ሴት አቀራረቧ አመስግና ለመመስገን ስለነበር ለውዳሴ ከንቱ ስለነበር አመጣጧን አይቶ መለሳት እንግዲህ አንቺም ቃሌን ሰምተሽ ብጠብቂው ብፅዕይት ትሆኛለሽ ሊላት ወዶ እንጂ አንዳች ተቃውሞ አናገኝበትም።



www.ethiopianorthodox.org